# አረጋውያን

# የመጓጓዣ አማራጮችዎትን ይመልከቱ/ ይወቁ

ለሁሉም አረጋውያን

**Connect-A-Ride፡- ስለ ሁሉም የመጓጓዣ አማራጮች ነፃ መረጃዎችን ያግኙ።**

- የእርስዎን ፍላጎቶች እና ስጋቶች ለመወያየት በ 301-738-3252 ይደውሉ ወይም በሚከተለው የኢሜል አድራሻ ኢሜል ያድርጉ። ConnectARide@AccessJCA.org
- የህዝብ አውቶቡሶችን እና የሜትሮ ባቡር (የምድር ውስጥ ባቡርን) እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ይጠይቁ።
- በበጎ ፈቃደኞች የሚሰጡ የነፃ ወይም የዝቅተኛ ዋጋ መጓጓዣ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይወቁ።
- በመረጡት ቋንቋ አገልግሎት እንዲያገኙ በሚደውሉበት ወይም መልክት በሚያስቀምጡበት ወቅት ቋንቋዎን ይናገሩ።

**ራይድ ኦን እና አንዳንድ ሜትሮ አውቶቡሶች ፣ በካውንቲው ውስጥ ነፃ እና በቀላሉ የሚገኙ መጓጓዣዎችን ይጠቀሙ።**

- ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኛ ነዋሪዎች ነፃ።
- ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ እና የአረጋውያን ስማርት ትሪፕ (Senior SmarTrip) ካርድ ያላቸው ወይም የሜዲኬር ካርድ ከፎቶ መታወቂያ ጋር ያላቸው መሆን አለባቸው።
- ካርድዎን ለአውቶቡስ ሾፌሮች ያሳዩ። በክፍያ ሳጥኑ ላይ አያስነኩት።
- የስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርዶች በሕዝብ ቤተ መጻሕፍት በ2 ዶላር ይሸጣሉ። ለመግዛት የእድሜ ማስረጃ ይዘው ይምጡ።
- የበለጠ ለማወቅ በ 311 ይደውሉ።

**የአዛውንቶች ማእከል መጓጓዣ፣ ወደ አካባቢዎ የአዛውንቶች ማእከል በነጻ ይጓጓዙ።**

- አውቶቡሶች ወደ አንዳንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበረሰብ ማእከላትም ይሄዳሉ።
- አገልግሎቱ በማዕከሉ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ይሰጣል።
- ለዝርዝር መረጃ ለየሞንትጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ አገልግሎት በ 240-777-4925 ይደውሉ።

---

ብቁ ለሆኑ አረጋውያን

**የሜትሮ አክሰስ እና ሴም ደይ አክሰስ ፣ ወደ ሚፈልጉበት ቦታ ለመሄድ ይጠቀሙ።**

- ቋሚ የአውቶቡስ መስመሮችን ለመጠቀም ችግር ያለባቸው ሰዎች ለአቅራቢያ መንገድ ዳር (curbside) አገልግሎት ማመልከት ይችላሉ።
- ለሜትሮ አክሰስ፣ ለካውንቲው ሴም ደይ አክሰስ ፕሮግራም እና ለሌሎች አማራጮች ለማመልከት እገዛ ለማግኘት ለ Connect-A-Ride በ 301-738-3252 ይደውሉ ።

**የታጀበ / የታገዘ መጓጓዣ፣ በአካል ጉዳት እና በገቢ ላይ ተመስርቶ ለአዋቂዎች አገልግሎቱ ይሰጣል።**

- ከእርስዎ ጋር የሚጓዝ ሰው ከፈለጉ በ 301-738-3252 ለ Connect-A-Ride ይደውሉ።

**Call-n-Ride ፣ ቅናሽ ታክሲ ከ63 ዓመት በላይ ለሆኑ አዋቂዎች እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ።**

- ጉዞዎ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ለማንኛውም ዓላማ ሊሆን ይችላል እንዲሁም ለህክምና ምክንያቶች ከካውንቲው ውጭ ያሉ ቦታዎችን መምረጥ ይችላሉ።
- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አካል ጉዳተኞችም ብቁ ናቸው።
- ለዝርዝር መረጃ ለ call-n-Ride በ 301-948-5409 ይደውሉ።

**ለኦንላይን መረጃ፣ የትራንስፖርት ኔትወርክ ማውጫውን በሚከተለው ድህረ-ገፅ ላይ ይመልከቱ። www.montgomerycountymd.gov/tnd**

MONTGOMERY COUNTY MARYLAND 1776

የዚህ ሰነድ አማራጭ ቅርጸች ሲጠየቁ ይገኛሉ። ለእርጅና እና የአካል ጉዳት አገልግሎቶች በ 240-777-3000 ይደውሉ።
መደበኛ ስልኮችን መጠቀም የማይችሉ ሰዎች ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ጋር ሲገናኙ ሜሪላንድ ሪሌይ 711 እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።